# የመጨረሻው ሰዓት

## ዓይን ያወጣ ጭፍጨፋ የአምባገነኖች የውድቀት ምልክት ነው

በዓለም ታሪክ እንደታየው አምባገነኖች በመጀመሪያው ላይ ሕዝብን በፍርሃት ለማንበርከክ ሃይልን ይጠቀማሉ፤ተቃውሞና እምቢባይነት ሲበረታባቸውና ወደመውደቁ አቅጣጫ ሲያመሩ በቁጭትና በብስጭት በበቀል የሚዘገንን እርምጃ ይወስዳሉ።በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የሂትለርን ታሪክ ብንመለከት ሲነሳ የብዙ አገሮችን ድንበር እየጣሰ በጦር ሃይል ለማንበርከክ ሞክሮ ነበር፣አልሳካለት ሲል በመጨረሻው ሰዓት ያደረበት ብስጭት ወደ እብደት ተለውጦ አይሁዶችንና ተቃዋሚዎቹን ሰብስቦ እንደ እንጨት አቃጥሎና በጋዝ አፍኖ ጨረሳቸው፤ከጥቂት ቀናትም በኋላ እራሱን አጠፋና ውድቀቱ ተረጋገጠ።

በኢትዮጵያ መሬት የዜጎች ደም በግፍ ሲፈስ በወያኔ ጊዜ መጀመሪያው አይደለም።በተለያዩ ጊዜያቶች በውጭና በውስጥ ጸረ ሕዝብ ጠላቶችና አምባገነኖች ሲፈጸም የነበረና ያለ፣የተለመደ ወንጀል ነው።ከጣልያን ወረራ ወዲህ አገር በቀሎቹ አምባገነኖች ሁሉ እንደ ባህልና መብት አድርገው ወስደውታል። የዛሬ ሃምሳ አምስት ዓመት እነጄነራል መንግሥቱ ነዋይ መፈንቅለ መንግሥት አድርገው አለመሳካቱን ሲያረጋግጡና ከሞትን አይቀር በሚል ደም ፍላት በእጃቸው ስር አስረው ያስቀመጧቸውን የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣኖች በረድፍ አሰልፈው እረሸኗቸው።በዚያ ጭፍጨፋ ለአገሪቱ ብዙ የደከሙ፣በጣሊያን ወረራ ጊዜ በርሃ ገብተው ለአገር ነጻነት የታገሉ አርበኞች ይገኙበታል። በዚህ ወቅት የወታደሩ ክፍል ተከፋፍሎ ደጋፊና ተቃዋሚ በመሆን ሚና ለይቶ ተጋደለ።ጥቂቶችም የአድማው መሪዎች በዚሁ የእርስበርስ ውጊያ ተመቱ፤አስከሬናቸው በየአደባባዩ ላይ ለቀናት ተዘርሮ ሰነበተ።ሌሎቹም በተለይም በዋና መሪነት ግልበጣውን ከወንድማቸው ከገርማሜ ነዋይ ጋር ያዘጋጁት የክብር ዘበኛው አዛዥ ጀነራል መንግሥቱ ነዋይ ቆስለው በሕይወት በመያዛቸው የንጉሱ መንግሥት ከተረጋጋ በኋላ በፍርድ ቤት ቀርበው የሞት ቅጣት ተበይኖባቸው ተክለሃይማኖት አደባባይ ላይ በስቅላት ተቀጡ።

የዛሬ አርባ ሁለት ዓመት የአቶ እንዳልካቸው መኮንን ካቢኔ ሥልጣኑን ለማደላደል በሚውተረተርበት ወቅት የሕዝብ ተቃውሞ አገርሽቶበት በከርቸሌ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙ ሳይቀሩ ለመብታቸው በመነሳት ጥያቄ ሲያቀርቡና የእስር ቤቱን አስተዳደር ሲቃወሙ፣በእስርቤቱ ጠባቂ ፖሊሶች በግፍ ተረሸኑ፤የብዙ ሰው ሕይወት ጠፋ።ለዚያ የግፍ ጭፍጨፋ መንግሥት የሰጠው መልስ እስር ቤት ሰብረው ሊወጡ የሞከሩ ወንጀለኞች ላይ እርምጃ እንደተወሰደ የሚገልጽ ነበር።የአቶ እንዳልካቸውን ካቢኔም አልቆየም ከሥልጣኑ በወታደሮች ቡድን ተወግዶ አብዛኞቹ ባለሥልጣኖች ጋር ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። በተፈጠረው ክፍተት ተጠቅሞ የሥልጣን እርካቡን ከሕዝቡ ፍላጎት ውጭ በመንጠቅ ደርግ የተባለው ሰውበላ የወታደር መንጋ በቦታው ተተካ።ይኸው ቡድን ሲነሳ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል ቃለ ተስፋ ቢሆንም ውሎ ሳያድር አገሪቱን በደም አጨቀያት። በተነሳበት የሕዝብና የወታደር ተቃውሞ በአደባባይ በግፍ ብዙ ሰዎችን እረፈረፈ፤ተቃውሞው አገር አቀፍ እየሆነ ሲመጣ በውስጡ መረበሽና ተስፋ መቁረጥ ሰፈነ።ቡድኑ ከሕዝቡ አልፎ እንዲመሩት ቀዳሚ ሊቀመንበርና እርእሰብሔር አድርጎ ከመረጣቸው ጄነራል አማን አምዶም ጋር ተፋጠጠ።በአንዳንድ የወታደር ክፍሎች በተለይም በአርሚ አቪየሽንና በመሃንዲስ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ከመፈታተን ደረጃ ላይ ሲደርስ ባልተጠበቀ ከቦ የማጥቃት እርምጃ ብዙዎችን ገሎ ሌሎቹን አስሮ በቁጥጥሩ ስር አደረጋቸው።

ተቃውሞው ግን አልበረደም ነበር።በተለይም ከጄነራሉ ጋር የተፈጠረው ፍጥጫ ከወሳኝ ደረጃ ላይ በመድረሱ በደርግ ዙሪያ ትልቅ ስጋትና ሽብር ተፈጠረ፤የጄነራሉ እምቢተኛነት በወታደሩ ውስጥ ካላቸው እውቅናና ክብር ከጀርባው ያሰለፈ ሃይል ሊኖር ይችላል የሚለው ስጋት እየጎላ መጣ።ጄነራሉን በማባበል ለማለሳለስ የተደረገው ጥረት ፍሬያማ ባለመሆኑ ከመቀደም መቅደም በሚል ስልት፣ጄነራሉን ከሚኖሩበት ቤት በመክበብ በተደረገ የተኩስ ልውውጥ ገደላቸው።ይህ እርምጃ ሊያስከትል የሚችለው ዋጋ ከፍተኛ ሆኖ ስለታያቸው፣ብሎም የተስፋ መቁረጥና የእብደት ስሜት ስላደረረባቸው ከነጄነራል መንግሥቱ ነዋይ ተመክሮ በመውሰድ ከሞትን አይቀር ሁሉንም በእጃችን ስር ያሉትን ገለን እንሙት ከሚለው ውሳኔ ላይ ደርሰው በገፍ ሰብስበው በአሰሯቸው ሃምሳ ሶስት የቀድሞ ባለሥልጣኖችና ሰባት ከወታደሩ የተውጣጡ ተቃዋሚዎቹ ላይ የሚዘገንን የግድያ እርምጃ ወስደው አገር አቀፍ ድንጋጤና ፍርሃት አሰፈኑበት።በወታደሩም ውስጥ ድፍረት ሳይሆን ሽብር ለቀቀበት።ይነሳብናል ብለው የጠበቁት የበቀል እጅ ሳይነሳ በመቅረቱ ለአስራሰባት ዓመት የአምባገነኖች የፍርሃት ድባብ መስፈንና የሕዝቡን ስነልቦና የሰበረ አረመኔያዊና ኢሰብአዊ አድራጎት እንዲቀጥል ያበረታታ ነበር።ደርግ በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ በአገሪቱና በሕዝቡ ላይ ያደረሰው በደል በአጭሩ ተነግሮ አያልቅም።በየወቅቱ በሕዝቡና በራሱ ውስጥ የተነሱትን ተቃዋሚዎች ፍጹም አረመኔያዊ በሆነ የግድያ እርምጃ አሶገደ።በነጄነራል ተፈሪ በንቲ፣በነኮሎኔል አጥናፉ አባተ ላይ የተወሰደው የግድያ እርምጃ የዚህ አካል ነው።ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን የበረደ ቢመስልም በሕዝቡና በወታደሩ ውስጥ የነበረው ተቃውሞ ውስጥ ውስጡን ይብላላ ነበር እንጂ አልቆመም። በመጨረሻው ሰዓት ላይ በ1982 ዓ.ም. በከፍተኛ የጦር መኮንኖች የተወጠነ አድማና የመገልበጥ ሙከራ ተደረገ።ምንም እንኳን ቢሳካ ኖሮ የተሻለ ለውጥ ይመጣ ነበር ብሎ መገመት ባይቻልም ሆኖም ግን ያም ከዝግጅት ድክመት የተነሳ ሳይሳካ ቀረና ከተሳተፉት መካከል ብዙዎቹ ተይዘው ካለፍርድ በመንግሥቱ ሃይለማርያም ውሳኔ በአንድ ሌሊት ከአስራአምስት የሚበልጡ ጄነራሎችና ከአርባ በላይ በጠቅላላው ከስልሳ የማያንሱ ከፍተኛ መኮንኖች ተረሸኑ። ይህ መውደቅን ያበሰረ የመጨረሻው ሰዓት አድራጎት ነበር።ዓመት ሳይሞላው ደርግ የተባለው በደም የበሰበሰው ስርዓት ፈራርሶ እንደጉም ተበተነ።

ከአስራ ሰባት ዓመት በኋላ በተቃዋሚ ስም፣ከጫካ ተንደርድሮ ቤተመንግሥት የገባው ቡድን በደርግ የተፈጸመውን የግፍ ጭፍጨፋ በጊዜው ከሚቃወምባቸው ነጥቦች ዋናውና አንዱ ነበር።ስልጣኑን ሲረከብ ግን በነጮቹ መንግሥታት በተለይም በእንግሊዝና በአሜሪካኖቹ ተሳትፎ በተደረገው ድርድር በደርግ ዘመነመንግሥት በገፍ የሕዝብ ደም ያፈሰሱት ብዙዎቹ ከዋናው ተጠያቂ ከአረመኔው መንግሥቱ ሃ/ማርያም ጭምር ወደ ፈለጉበት አገር እንዲወጡ አደረገ።ሕዝቡን ለማወናበድ ጥቂቶችን ይዞ እስር ቤት አጉሮ ለይስሙላ ለፍርድ አቀረበ።በዛን ጊዜ ከዓለም ማህበረሰብ ተብየው ስብስብ ለቀረበበት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ " ሕዝብ የበቀል እርምጃ እንዳይወስድባቸው ለራሳቸው ደህንነት ሲባል የተደረገ እርምጃ ነው" የሚል ነበር።እንዳለውም ከጥቂት ዓመታት እስራት በኋላ ጥፋታቸውን አምነው ሕዝቡን ይቅርታ ሳይጠይቁ ሁሉንም በነጻ ለቀቀ። የተግባር አንድነቱን አሳዬ።የህዝቡ ደምም በከንቱ ፈሶ ቀረ።ተጠያቂዎቹም በየአገሩ ባሰደዱት ህብረተሰብ መሃል ገብተው፣ስደተኛ በመሆን በስደተኛ ወንበር ላይ

ተቀምጠው የተደላደለ ኑሯቸውን ቀጠሉ።በፈጸሙት ግፍ በመጸጸት ፈንታ እየተኩራሩ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል እንዲሉ የፈጸሙት ወንጀል ተገቢና ሕጋዊ አድርገው በመከራከር መጽሃፍ ጽፈው የገበያ ሸቀጥ አደረጉት።በሥልጣን ዘመናቸው የኢትዮጵያውያኑን ሕይወት እንደበዘበዙት ሁሉ በስደት ዘመናቸውም ገንዘቡንም በዘበዙት።

የወያኔ ባለሥልጣኖች ከደርግ ባለሥልጣኖች የሚለዩበት ነገር ቢኖር ቢወገዱ በስደተኛ ሳይሆን በየአገሩ ኢንቬስተር በመሆን የሚኖሩበትን የገንዘብ አቅም ማካበታቸውና ማዘጋጀታቸው ነው።በሂደትም በመታየት ላይ ያለው ይኸው ነው።ልጆቻቸውንና ቤተሰባቸውን ቀድመው በማሶጣትና ቤትና ቋሚ ንብረት በመግዛት ፣በየኩባንያው የሽርክናና ባለቤትነት ድርሻ (share) በመያዝ የወደፊት ኑሯቸውን አደላድለዋል።በሚሊየን ከዛም በላይ የሚቆጠር ዶላር የሌለው ባለሥልጣን የለም።ማንኛውም አገር ባዶ እጁን የሚመጣ ስደተኛን እንጂ ብር ተሸክሞ የሚመጣን ወንጀለኛ አይጠላም፣ የወጡትን እጁን ዘርግቶ ተቀብሏቸዋል፣የቀሩትንም ሲወጡ በክብር ይቀበላቸዋል።ሰብአዊ መብት ጥሳችኋል፣ ሕዝብ ገላችኋል፣አገር ዘርፋችኋል፣ወንጀለኞች ናችሁ ብሎ አይጠያቃቸውም።

የወያኔ ዘረኛ ቡድን ከደርግ የሚለየው ነገር ቢኖር በዘር ደረጃ የተዋቀረ መሆኑ እንጂ በሥልጣን አያያዙና በሚከተለው  መመሪያው አይደለም።ሁለቱም ጸረ ሕዝብና አምባገነንነትን የሚከተሉ ቡድኖች ናቸው።ደርግ ተቃዋሚውን  አናርኪስት/ስርዓተ አልበኛ፣የአሮጌው ስርዓት ናፋቂ፣...በማለት ያሳድድ፣ይገል፣ያስር ነበር።በዚህ ስልት ሕዝቡ በፍርሃት ለአስራ ሰባት ዓመት የእሳት ሰንሰለት ተሸክሞ ኖረ።እሱንም ተክቶ አሁን በስልጣን ላይ ያለው ቡድን በተመሳሳይ ደረጃ ላለፉት ሃያ አምስት አመታት ተቃዋሚውንና ለመብቱ የቆመውን ማሳደድ ስራዬ ብሎ ያዘው።ብዙዎችን አሳደደ፣አሰረ፣ገደለ። ለሚወስደው ጨካኝ እርምጃው የሰጠው ምክንያት የአገርን አንድነት የሚያናጋ፣ሰላምና እድገትን የሚጻረር ተግባር ላይ የተሰማሩ፣የደርግና የቀድሞ ስርዓት ደጋፊዎች፣ አቀንቃኞች፣ነፍጠኞች፣አሸባሪዎች  የሚል ነው።በዚህ አረመኔያዊ አገዛዝ እጅ የብዙሃን ደም በሜዳ ላይ ፈሰሰ፣ገዳዮችም ተሾሙበት፣ተሸለሙበት።ፍትህና ሕግ ትርጉሙን አጣ።የአገራችን መሬት የደም ገንዳ/አሸንዳ ሆነ።

በተከታታይ ለፈጸመው ወንጀል ባለመጠየቁ በአጉል እብሪት አሁንም ግድያውን ሥራዬ ብሎ ቀጠለበት።ላለፉት አስር ወራት በኦሮሞው ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የግፍ መረቡን ዘርግቶ በጠራራ በየአውራ መንገዱ አያሌ ህይወት አጠፋ፣ብዙዎች ቆሰሉ፣ታፍሰው በየእስርቤቱ ተወረወሩ።በአደባባይ የፈጸመው ግፍ አልበቃ ብሎት  አሁን የሕዝብ ትግል በየቦታው ሲቀጣጠልና የመገርሰሱ አደጋ ገሃድ እየሆነ ሲመጣ፣ በደም ፍላትና ተስፋ መቁረጥ በአዘዞ፣በደብረ ታቦር፣ በጎንደር፣በአምቦ፣ በቂሊንጦ እስር ቤት ውስጥ በእጁ ላይ ያሉትን እስረኞች በእሳትና በመትረየስ ፈጃቸው።ይህን ግፍና አረመኔ ተግባር በስማቸው የሚነግድባቸው የትግራይ ተወላጆች አብዛኞዎቹ ከጥቂቶቹ በስተቀር በጸጋ የተቀበሉት በሚመስል መልኩ በዝምታ ተመለከቱት። በሌላው ላይ የሚደርሰው በደል፣የሌላው ቁስል እንደሰው ሳይሰማቸው ቀረ።በዚህም አላበቃም በየቦታው ድግስ እየደገሱ ወንጀለኛውን መንግሥታቸውን እየጨፈሩ አሞገሱት፣ሕዝቡን ተሳለቁበት፣ ዛቱበት። ይበልጥም ጥላቻው እንዲበዛ የሚደግፉት መንግሥት በራሳቸው ላይ ወንጀል እየፈጸመ ሌላው በጥላቻ የፈጸመባቸው በማስመሰል የሚነዛውን ወሬ አሜን ብለው ተቀበሉት።ቀጣዩ የአረመኔው መንግሥት እርምጃ በየቦታው ቦምብ በመወርወር ጥቃቶችን በስውር እያከሄደ ሌላውን በመወንጀል ብዙ ሕዝብ ለመፍጀትና አገሪቱን የበለጠ ቀውስ ውስጥ ለመክተት እንደሆነ የታ ድርጊትና ሾልኮ የወጣው መረጃ ያረጋግጣሉ።

ለአለፉት ሃምሳ ዓመታት የተደረጉት የግፍ ጭፍጨፋዎች በተለይም በእስራት ላይ ባሉ አቅመቢስ በሆኑት ዜጎች ላይ የሚወሰደው የግድያ ውሳኔ የአምባገነኖች የእብደት ባህርይ፣ የተስፋ መቁረጥና የመጨረሻው ሰዓት ምልክት እንደሆነ እንረዳለን።

ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ቆመናል የሚሉት የውጭ አገር መንግሥታትም አይተው እንዳላዩና ሰምተው እንዳልሰሙ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው አለፉት።የዜና ተቃማቱና ጋዜጠኞችም በከተማቸው አንድ ውሻ መኪና ገጭቶት ቢቆስል በየዜና መድረኩ የሚያስተጋቡትን ያህል ቀርቶ የግማሹን ያህል እንኳን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተፈጸመውንና በመፈጸምም ላይ ያለውን ጭፍጨፋ ለደቂቃም ትኩረት አልሰጡትም።ዜጎቻቸው በሚያካሂዱት ንብረት ላይ አደጋ ሲደርስ ብቻ ያስተጋባሉ።መንግሥታቱ ተደጋግሞ ለቀረበላቸው አቤቱታም ደንታ አልሰጡትም፣እንደውም ምርጫቸው የንጹሃን ደም የሚያፈሰውን አረመኔ ስርዓት መርዳትና መንከባከብ  ነው።

ከጥቂት ጊዜ ወዲህ የሕዝቡ ትግል እየገፋ ሲመጣ   ሁለት ባላ ትክል አንዱ ቢሰበር ባንዱ ተንጠልጠል እንዲሉ ከወያኔ ያልተሻሉና ለጥቅማቸው የቆሙ ቡድኖችን በማሰባሰብ የጥገና ለውጥ እንዲደረግ ሙከራ በመደረግ ላይ ነው የሚለው ወሬ በስፋት ይነገራል።በአሜሪካና በአውሮፓ መሪዎች  የፖለቲካ  ማድቤት የሚፈተፈተው ድግስ  ይህን የሚመስል ነው።ምርጫቸው ያለው መንግሥት ተጠግኖ እንዲቀጥል ሲሆን የሕዝቡ ትግል ከቀጠለና የወያኔ ዕድሜ የሚያጥር መስሎ ከታያቸው በሌላ መሰል አገልጋይ ቡድን እንዲተካ ማድረግ ነው።በምንም መንገድ የአገሩን ጥቅም አሳልፎ የማይሰጥ አገር ወዳድ የሕዝብ መንግሥት እንዲመጣ አይፈልጉም።በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ መንግሥት መምጣት ማለት ሌላውን የአፍሪካ ሕዝብ ለዳግመኛ አልገዛም ባይነትና ጸረ ብዝበዛ ለውጥ የሚቀሰቅስ ስለሚሆን እንዳይሳካ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ።

በቅርቡ በአውሮፓ ማህበር/ፓርላማ/ ጣራ ስር አንድ ስብሰባ ተጠርቶ ነበር፡፤ስብሰባውን የጠሩት አና ጎመሽ የተባሉት የፖርቱጋል ሶሻሊስት ፓርቲ ተጠሪ ሲሆኑ በቢሮዋቸው ባደረጉት በዚህ ስብሰባ ላይ በቅርብ የሚያውቋቸው ሌሎች የአውሮፓ ፓርላማ አባላት ተገኝተው ነበር።በዚህ ስብሰባ ላይ ከኢትዮጵያውያኑ በኩል ከተጋበዙት አብዛኛዎቹ በጎሳ የተደራጁት ናቸው።ከነዚህም ውስጥ፣የኦሮሞ፣የአፋር፣የሲዳማ፣የኦጋዴን፣ወዘተ ድርጅት ተወካዮች ሲሆኑ በአገር አቀፍ ትግልና በአንድነት ሃይሉ ጎራ የተሰለፉ ግለሰቦችም ተካፍለው በአጠቃላይ በአገሪቱ ያለውን ሁኔታ ለማስረዳት ሞክረዋል። አገር አቀፍ አቋም ያላቸው አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች ግን  አልተሳተፉበትም። የስብሰባ መካሄድ ለጥቂቶች  በምስጢር የተላለፈ ጥሪ ነበር ማለት ይቻላል።በስብሰባው ላይ የተሳተፉትአብዛኛዎቹ ችግሩ አገር አቀፍ እንደሆነ ቢገልጹም በተደጋጋሚ በተናጠልም ሆነ በጋራ የሚያቀርቡት  አቤቱታ መንግሥት በሕገመንግሥቱ የሰፈረውን የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና የማስተዳደር መብት አላከበረም የሚል ነው፤ይህ ማለት በአንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ ስር የተቀመጠው መብት ሙሉ ለሙሉ አልተከበረልንም (የመገንጠልን መብት ጨምሮ) ማለት ነው።እንደሚታወቀው የከባቢ አስተዳደሩን የተረከቡና በሌላው ተወላጅ ነዋሪ ላይ የፈለጉትን እንዳደረጉና በማድረግም ላይ እንዳሉ አይካድም።ግን በዚያ ብቻ የረኩ አይመስልም።ከወያኔ ጋር ያላቸው ትንቅንቅ ሙሉ ለሙሉ አንቀጹ ተግባራዊ ይሁን በሚል ዙሪያ እንደሆነ የፖለቲካ አቅጣጫ የሚከታተል ሊገነዘበው ይችላል።ከወያኔ ጋር በብዙ ሲስማሙ

የሚለያዩበት የአንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ አተረጓጎም ላይ ብቻ ነው። አሁን በዚህ ስብሰባ ላይ አቀራረባቸውን በመለወጥ የለዘበ አቋም የሚከተሉ መስለው በስብሰባውና ከስብሰባው በኋላ ለጀርመን ራዲዮ ዘጋቢ በሰጡት ማብራሪያ ለማሳየት ሞክረዋል።በቦታው በነበሩ ታዛቢዎች አስተያየት ግን የዓላማ ለውጥ  አድርገው ሳይሆን ያደረጉት የስልት ለውጥ ነው ሲሉ ተችተዋል።ቂጣም እንደሁ ይጠፋል ሽልም እንደሁ ይገፋል ነውና  የወደፊቱን የምናየው ይሆናል።

ይህ ስብሰባ በአውሮፓ ፓርላማ እውቅና ያገኘና የተዘጋጀ ሳይሆን በአንድ ግለሰብ በአና ጎመሽ አነሳሽነት የተደረገ እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ ነው።በስብሰባው ላይ የተገኙት አንዳንዶቹ የፓርላማ አባላት  የአገራቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅላቸው አማራጭ በማጣታቸው የተቸገሩ እንደነበረና አሁን ግን በዚህ ስብሰባ ምልክት እያዩ መምጣታቸውንና በየመንግሥታቸው በኩልም የተቻላቸውን ለማድረግ እንደሚሞክሩ ተናግረዋል። ወይዘሮ አና ጎመሽ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለረጅም ጊዜ ትኩረት የሰጡና በአውሮፓ ፓርላማ ውስጥ ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ግለሰብ ናቸው።የአሁኑም እርምጃቸው ሌሎቹ የፓርላማ አባላት ግንዛቤ አግኝተው ከጎናቸው እንዲቆሙ ለማድረግ ነው።ይህ ሂደት ግን በአንዳንዶቹ ኢትዮጵያውያን በኩል የአውሮፓ ፓርላማ ተሰብስቦ በኢትዮጵያ ላይ ውሳኔ እንዳስተላለፈ ተደርጎ ሲናፈስ ተስተውሏል፤ይህ እራሱ የአውሮፓን ገጽና አቋም በተሳሳተ መልኩ እንዲታይና ኢትዮጵያውያኑ ከትግላቸው ይልቅ በውጭ ሃይል እንዲተማመኑና ተስፋ እንዲጥሉ የሚያደርግና የሚያማልል ነው።እነሱ የሚፈልጉት ጥቅማቸው መጠበቁን እንጂ የኢትዮጵያ አንድነት መከበሩን፣የ ዴሞክራሲ ስርዓት መስፈኑን አይደለም። በማንኛውም ስርዓት ስር ቢሆን፣ በትልቋ ኢትዮጵያም ይሁን በተበጣጠሰች ኢትዮጵያ የሚፈልጉትን ካገኙ ዓይናቸውን አያሹም፤እንደውም በተዳከመ ደረጃ ላይ ባለ አገር ውስጥ የሚኖራቸው ቁጥጥር የባሰ ይሆናል።ስለሆነም በእነሱ ላይ ተስፋ መጣልና እንደአማራጭ ለሚያዋቅሩት ስብስብ በር መክፈት ወይም አሁን በሚካሄደው የወያኔ አረመኔ ተግባር ተደናግጦና ፈርቶ ከትግሉ ማገፈግፈግ ለቀጣይ ጥፋት እድል መስጠት ይሆናል። የተከፈለው መስዋእትነት ተከፍሎ የተጀመረው  ኢትዮጵያን አድኖ ለተሻለ ስርዓት የሚያበቃውን ትግል ከዳር እንዲደርስ ሁሉም ለውጥ ፈላጊ የቻለውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል። በሽርፍራፊ የጥገና ለውጥ አረመኔው ቡድን እንዲቀጥል ወይም ከሕግ ተጠያቂነት እንዲሰወር ማድረግ ወይም በተመሳሳይ መንገድ የጎሳ ስብስብ የሆነ አዲስ መጥ አምባገነን ቡድን በተራው እንዲገዛ መፍቀድ ስህተት ብቻም ሳይሆን በራስ ላይ መፍረድ ነው።ለሁሉም የሚበጀው ሰብአዊነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር ማድረግ ነው፤በዚያን ጊዜ የሁሉም ጥያቄና መብት መልስ ያገኛል፤ይከበራልም።የጎሳ መብት መከበር ማለት የሁሉም ሰው መብት የሚከበርበት ማለት አይደለም፤አለመሆኑንም በሽርፍራፊው የጎሳ መብትና አስተዳደር እያየነው ነው።

በሁሉም ኢትዮጵያውያን ምርጫ እንጂ በጥቂት ጎሰኞችና በውጭ ሃይሎች እርዳታ፣ፈቃድና ፍላጎት የምናድርበት ጊዜ ማክተም አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው አማራጭ አንድ ነው።ተባብሮ መታገል! ለዚያም በየፊናው የሚታየው በክልልና ጎሳዊ ስሜት በተናጠል የራስን ጥቅም የማስከበሩ እሩጫ መቆም ይኖርበታል።ተቃዋሚ ነን የሚሉ የፖለቲካ ቡድኖች/ድርጅቶች ተባብረው ከሕዝቡ ጋር ተሰልፈው አመራር ሊሰጡ ይገባል።የሕዝቡን ትግል የነሱ ከውጭ አገር መንግሥታትና ከአረመኔው መንግሥት ጋር  ለሥልጣን የመደራደሪያ ዕድል አድርገው መጠቀም አይገባቸውም።ፊታቸውን ወደ ሕዝባቸው መመለስ ይኖርባቸዋል። ለውጭ መንግሥታት እኔ ከአለው መንግሥት የምሻል የጥቅማችሁ አስከባሪ እሆናለሁ ብሎ እራስን ማዋረድና ለባርነት የማጨት አዝማሚያ መቆም አለበት አለበት።በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን ለሥልጣን እንዳበቁትና ለቀውሱና ጥፋቱ ሁሉ ተጠያቂዎች እንደሆኑ እየታወቀ እነሱን መማጸን አያዋጣም፤የሚያዋጣው በራስ መተማመንና የተበታተነውን ሃይል ሰብስቦ ማታገሉ ነው።ለስልጣን ከሚደረገው ሽኩቻ ይበልጥ አገርና ሕዝብ የማዳኑ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

1.በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ለኢትዮጵያ አንድነትና ለተሻለ ስርዓት የሚደረገውን ሕዝባዊ ትግል በዲፕሎማሲና በቁስ መርዳት፣

2.ለቆሰለው ሕክምና ለተፈናቀለው መቋቋሚያ፣ለታሰረው ስንቅ፣ማቅረብ  የሚችል አንድ የክፉ ቀን ፈጥኖ ደራሽ የሆነ ብሔራዊ የእርዳታ አስተባባሪ አካል በአስቸኳይ ማቋቋም።በየቦታው በልዩልዩ ስም የሚደረገው ጥረት መልካም ቢሆንም የበለጠ ፍሬያማ ለማድረግ ወደ አንድ ብሔራዊ ተቋም ቢሰባሰብ የተሻለ ይሆናል።

3.በተጨማሪም ሰብአዊ መብት ሲረገጥና ሕግ ሲጣስ የሚከራከርና የሕዝቡን መብት የሚያስከብር የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ማቋቋም ወይም የተቋቋመ ካለ ማጠናከር፣ከሰብአዊ መብት አስከባሪ ተቋማት ጋር ተባብሮ መስራት የሚቻልበትን ዘዴ መንደፍ፣

4.የተዛባ ዜና ከማቅረብ የራቀ ታማኝነት ያለው የሕዝብ ድምጽ የሆነ የሚዲያ አሰራር መሟላት፣ የሶሻል ሚዲያዎችን በስፋት መጠቀም፣

ከዚህ በላይ የተገለጹትንና ሌላውንም አስፈላጊ ተግባር ለማከናወን በውጭ አገር የሚገኙትንና በተናጠል የሚንቀሳቀሱትን ስብስቦችና ማህበራትን በማቀናጀት በተባባረ ጉዞ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የሚችል እነሱን ያካተተ ማእከል መፈጠር አስፈላጊና ወቅታዊ ነው። በየቦታው ያሉት ስብስቦች ይብዛም ይነስም ብዙ ተግባራትን እንዳከናወኑ መካድና መዘንጋት አይገባም።እነሱን ማጠናከር እንጂ ከነሱ የተለዩ ሌላ እንደ አዲስ ለመጀመር መነሳትም ጊዜ ከማባከኑም ባሻገር አላስፈላጊ አለመግባባት ሊፈጥር ይችላል።ጥረታቸው እንዲሰምርና እንዲሳካ በጋራ የሚመራና ከአገር ቤቱ ትግል ጋር የሚያቀራኝ አካል ለመፍጠር የሚረዳ በአስቸኳይ ሁሉንም የሚያሳትፍ ጉባኤ መጥራት አስፈላጊ ነው።ጉባኤው የቅርብና የሩቅ ተግባራትን መርምሮ የሚያስቀምጥና በተግባር ሊተረጉሙ የሚችሉትን መርጦ አላፊነቱን የሚሰጥ ይሆናል።

ለድል ወይም ለውድቀት ከወሳኝ ሰዓት ላይ ደርሰናል!ከተባበርን እናሸንፋለን፣ካልተባበርን እንሸነፋለን።

አገሬ አዲስ